# ተዘጋጅተሃል/ተዘጋጅተሻል?

## ለድንገተኛ ጊዜ/የአደጋ ጊዜ

# ዝግጁነት

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ለተማሪዎቻችን እና ለሰራተኞቻችን ሠላምና ደህንነቱ የተጠበቀ እና አስደሳች የመማሪያ አካባቢ ለማቅረብ ቁርጠኛ ነው። በየዓመቱ ለአስቸኳይ ሁኔታ ተማሪዎች ዝግጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እያንዳንዱ የ MCPS ት/ቤት በርካታ የድንገተኛ አደጋ የቅድመ ዝግጅት ሙከራዎች ያካሄዳሉ።

## ከአማራጮች ጋር በዝግ ቦታ መሆን(መደበቅ)/Lockdown

ምን፡- ግለሰብ ወይም ግለሰቦች በጦር መሣሪያ ትምህርት ቤት ውስጥ አደጋ በሚያደርሱበት ሁኔታ በህግ አስከባሪዎች የተዘጋጀ የደህንነት ጥበቃ ሂደት። ሜሪላንድ ስለትምህርት የሠላም አስፈላጊነት ደንብ "Safe to Learn Act of 2018" ይህንን አዲስ የልምምድ ስልት/drill አውጥቷል።

እንዴት፡- ተማሪዎች እና ሰራተኞች ደህንነታቸውን ለመጠበቅ ከሚከተሉት ስትራተጂዎች ውስጥ በአንዱ እንዲሳተፉ ሁኔታዊ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ስልጥነዋል፡-

» ራሳቸውን በክፍል ውስጥ ወይም በር ቆልፈው እንዲቀመጡ፣ መስኮቶችን እንዲሸፍኑ፣ መብራቶቹን ማጥፋትና ቀጣይ መመሪያ እስኪተላለፍ ድረስ በዝምታ እንዲቆዩ።

» የትምህርት ቤት ሠራተኞች መመሪያ ሲሰጧቸው በፍጥነት ከት/ቤት ክልል ህንፃ ርቀው መሄድ።

» እድሜአቸው የሚፈቅድ ከሆነ፣ እንደ የመጨረሻ መፍትሄ ራሳቸውን ለመከላከል መዘጋጀት። ይህም ጥቃት ፈጻሚው(ዋ) የሚሠነዝረውን ለማደናቀፍ ወይም ጉዳት ለማድረስ አንድ ነገር መወርወርን ሊያካትት ይችላል።

ይህ አሠራር በተለምዶ "Lockdown" የተባለውን አሠራር ያጠናክራል።

## መልቀቅ/ጥሎ መውጣት

ምን፡- በህንፃው ውስጥ ለመቆየት በጣም አደገኛ በሚሆንበት ጊዜ ከትምህርት ቤት ለመውጣት ጥቅም ላይ የሚውል የደህንነት ሂደት (ለምሳሌ፡- እሳት፣ የጋዝ ሽታ፣ ወዘተ)

እንዴት፡- ተማሪዎች እና ሰራተኞች ከህንፃው ርቀው ወደ ተመደበ ቦታ ይወጣሉ። ምን ጊዜ ወደ ት/ቤት ተመልሶ ለመግባት እንደሚፈቀድ የህዝብ ደህንነት ኃላፊዎች ይወስናሉ።

## በቦታው መጠለል

ምን ፡- በትምህርት ቤት ዙርያ ባለዉ ማህበረሰብ ዉስጥ የህግ አስከባሪዎች የሚገቡበት ከባድ ክስተት ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ የአስቸኳይ ጊዜ አገልግሎት የህክምና ጉዳይ ወይም የተያዘ ክስተት መደናቀፍ የሌለበት መዳረሻ ሲያስፈልግ ስራ ላይ የሚዉል ደህንነት የመጠበቅ ሂደት። በተጠለሉበት ቦታ እያሉ መመሪያ በተከታታይ ይሰጣል።

እንዴት፡- ህንፃው ውስጥ በተፈጠረ ሁኔታ ባሉበት በተጠለሉበት ወቅት፣ ሁኔታው በአስቸኳይ ጊዜ ሠራተኞች እስከሚስተካከል ድረስ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍሎቻቸው ይቆያሉ (ወይም እንዲቆዩ በተፈቀደ ሥፍራ)። ክስተቱ የተፈጠረው በአካባቢ ማህበረሰብ ከሆነ፣ በውጪ የሚካሄድ እንቅስቃሴ ወደ ውስጥ መግባት እና የውጭ በሮችን መቆለፍ።



## በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች

# ከአማራጮች ጋር በዝግ ቦታ መሆን (መደበቅ)/LOCKDOWN

### ይህ የአደጋ ጊዜ ልምምድ ለምን አስፈላጊ ይሆናል?

ባለፈው ዓመት በትምህርት ቤት ውስጥ በተፈጠረው አሠቃቂ የተኩስ አደጋ ወቅት፣ ሜሪላንድ በመካሄድ ላይ ያለ የጥቃት አፈጻጸም የመከላከል ልምምድ እንዲገመገም/ክለሳ እንዲደረግ እና በህግ አስከባሪ እና በሌሎች የት/ቤት ዲስትሪክቶች በቅርብ የተሻሉ የአሠራር ለውጦች ጋር በተጣጣመ መልኩ መካሄድ ያለበትን "Safe to Learn Act of 2018" ደንብ አሳልፏል። ት/ቤቶች ዋነኛ ሠላምና ደህንነት ያለባቸው ሥፍራዎች መሆን እንዳለባቸው መረጃዎች ቢያመለክቱም፣ የትምህርት ቤቶቻችንን ሠላምና ደህንነት በንቃት መጠበቅ ይኖርብናል፡፡

### ከአማራጮች ጋር በዝግ ቦታ መሆን(መደበቅ)/Lockdown with Options እና ለዓመታት ስናደርገው የነበረ በዝግ ቦታ መሆን(መደበቅ)/Lockdown drill መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

*Lockdown with Options*ማለት በተለምዶ ሲደረግ የነበረውን lockdown procedure በሙከራዎች የተረጋገጡ ለውጦች ላይ ተመርኩዞ በይበልጥ የተሻሻለ አሠራር ነው። ጥቃት እየተሠነዘረ ባለበት ቦታ መወሰድ ያለበት የተሻለ አማራጭ በተቆለፈ ክፍል ውስጥ መቆየት ሲሆን፣ ተማሪዎች እና ሠራተኞች ወደ ክፍል ውስጥ ለመግባት በማይችሉበት ጊዜ Lockdown with Options የደህንነት ስትራቴጂዎችን ዝርዝር አማራጮችን ይሰጣል።

ስትራቴጂው የሚያካትተው፤ ለማድረግ ዕድሉ ካለ በፍጥነት ከትምህርት ቤት ክልል ውጭ መሸሽ/ማምለጥን ይጨምራል። የግዴታ ወይም ምንም አማራጭ ከጠፋ ሠራተኞች እና ተማሪዎች (እድሜ የሚፈቅድ ከሆነ) እንደ መጨረሻ እርምጃ ራሳቸውን ለመከላከል መዘጋጀት አለባቸው። ይሄ የሚያካትተው ጥቃት እየሠነዘረ ባለው/ባለችው ሰው ላይ ለምሣሌ፡- ወደ ክፍል ውስጥ ለመግባት ከቻለ ለማደናገር ወይም ጉዳት ለማድረስ የሆነ እቃ መወርወር ወይም በቀጥታ ጥቃት መፈጸም።

### ትምህርት ቤቶች መቼ ነው የመከላከል ልምምድ የሚያደርጉት?

ሁሉም የትምህርት ቤት ሠራተኞች በመጀመሪያው እና በሁለተኛው ሴሚስተሮች ስልጠና የሚሰጣቸዉ ሲሆን በተወሰኑ ትምህርት ቤቶች በሁለተኛው ሩብ ዓመት ወይም ሴሚስተር የተማሪዎች የስልጠና ልምምድ ይከተላል። የተማሪዎች ሥልጠና በሚሰጥበት ጊዜ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ለማህበረሰቡ ያሳውቃል።

### ተማሪዎች ህንፃውን ከለቀቁ፣ ወዴት ነው መሄድ ያለባቸው፣ እና መቼ መመለስ እንደሚኖርባቸውስ እንዴት ለማወቅ ይችላሉ?

የትምህርት ቤት ሠራተኞች በሚሰጧቸው መመሪያ መሠረት፣ ተማሪዎች በፍጥነት ከትምህርት ቤት ክልል ውጪ ርቀው ትምህርት ቤቱን ለማየት ወደማይችሉበት ርቀት መሸሽ አለባቸው። ትምህርት ቤቱን ለቀው የወጡ ተማሪዎች 911 መደወል አለባቸው እና የሚገኙበትን ቦታ ለቤተሰባቸውም መግለጽ አለባቸው። ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ ከትምህርት ቤቱ ርቀው መሸሽ አለባቸው፣ ነገር ግን ሠላም በሆነ ጊዜ ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ እንዲያስችላቸው በአቅራቢያ መሆናቸውን ተማሪዎች ክትትል ሊደረግባቸው ይገባል።

የተደቀነው አደጋ ካበቃ በኋላ፣ ፖሊስ ወይም ሠራተኞች ወደ ትምህርት ቤት ክልል ሄደው ተማሪዎች ወደ ክፍል እንዲመለሱ ለመንገር እና ተማሪዎችም በሚድያ የሚነገሩ ነገሮችን በሞባይሎቻቸው ማየት-ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል። MCPS በእንደዚህ ዓይነት ድንገተኛ አደጋ ወቅት ለመገናኛ የሚረዱ በርካታ apps እያፈላለገ ይገኛል።

### ተማሪዎች በበለጠ ንቁ ልምምድ መልኩ ከትምህርት ቤት እንዲሠወሩ ወይም እንዲሮጡ በማድረግ ፈንታ ለምንድነው ለተማሪዎች የስልጠና ክፍለጊዜያት ጊዜ የምንሰጠው?

*Lockdown with Options*ጭንቀት/ውጥረት፣ እና ስጋት ሊፈጥር የሚችል ከፍተኛ ለዉጥ ስለሆነ፣ ለአዳዲስ ፕሮቶኮሎች ሰራተኞች እና ተማሪዎችን እንዴት ማዘጋጀት እንዳለብን ማስተዋል ያስፈልገናል። በተጨማሪ፣ *Lockdown with Options*ስልጠና-ልምምድ ሠራተኞች እና ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ወይም በቢሮ ለመሠወር/ለመደበቅ ወይም ህንጻውን ለቀው ለመውጣት በፍጥነት መወሰን ይጠበቅባቸዋል። ይህ ዓይነት አስተሳሰብ ሁኔታዎችን ማጤን ተብሎ ይጠራል፤ ይህም የአንድ ሰው ስለአካባቢ-ዙሪያ ሊወስድ በሚችላቸው እርምጃዎች ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር አመለካከት እና ትንታኔ ነዉ። ከሠራተኞች እና ከተማሪዎች ጋር የሚደረገው ስልጠና የሚያተኩረው ሁኔታዎችን በማጤን ላይ ነው።